# የ2002 የ1ኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት

1. ሪፖርት ላኪ ዞን፡- ወላይታ ዞን አቅም ግንባታ መምሪያ

2. ሪፖርት የሚሸፍነው ጊዜ፡-   ከሐምሌ 1 እስከ መስከረም 30/2002 ዓ.ም

3. የታቀዱ ተግባራት

መግቢያ

ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት ኀብረተሰቡ በየደረጃው የልማቱ ባለቤትና ተጠቃሚ የሚሆንበት ሥርዓት ለመዘርጋት ፣ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት እንዲሁም መልካም አስተዳደርም ለማስፈንና የማስፈፀም አቅም ግንባታ እስትራቴጂያችን የሁሉንም ልማት ኃይሎች በማጎልበት የሚፈፀም ዕቅድ በመዘጋጀት እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል፡፡

በለውጥ ኘሮግራሞችና ኘሮጀክት ጥናትና ትግበራ የሥራ ሂደት

3 1 የታቀዱ ቁልፍ የትኩረት መስኮች

1. በሁሉም የመንግሥት ተቋማት የተጠናከረ ድጋፍና ክትትል በማድረግ የተተገበረ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ ፣
2. በሁሉም የመንግሥት ተቋማት የተዘረጋ ሚዛናዊ የውጤት ተኮር ዕቅድ /BSC/ አዘገጃጀትና አሠራር ፣
3. በዞን 12 ወረዳና በ3 ሪፎርም ከተሞች በሚገኙ 260 ሴክተሮች የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የተገልጋዮች ቅሬታ የሚስተናገድበት አሠራር ፣
4. በዞኑ በሁሉም ወረዳና ከተማ ቀበሌ መልካም አስተዳደር ፖኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘረጋና በተጠናከረ ሁኔታ ሥራ ላይ የዋለ የኢንስፔክሽን አደረጃጀትና አሠራር ከዞን እስከ ቀበሌ የተዘረጋና የተደራጀ አንድ የእንስፔክሽን የሱፐርቪዥን አሠራር ፣
5. በሁሉም የዞኑ 314 የቀበሌያት መዋቅር አሳምኖ ማሠራትን ለማጠናከር ምርጥ ስኬቶቻችንን ማስፋት ረገድ የተደረገ ድጋፍ ፣
6. በሁሉም ቀበሌያት የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ በተጠናከረ ተቋማዊ መዋቅር እንዲሠራ የተደረገ ክትትልና ድጋፍ ፣
7. በ314 ቀበሌያት የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ሥርዓት በመዘርጋት ረገድ የተደረገ ድጋፍና ክትትል ፣
8. በዞን 12 ወረዳና 3 ከተሞች ለሚገኙ ለፍትህ ተቋማት የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ

ኘሮግራም አተገባበር ተደራሽ ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ የተደረገ ደጋፋዊ ክትትል ፤

9. የኀ/ሰቡን ሠላምና ፀጥታን ለመጠበቅና ፈጣንና ፍትሀዊ አገ/ት ለመስጠት ከፍትህ አካላት ጋር በመቀናጀት የተዘረጋ ሥርዓት ፤

<u>የታቀዱ ዝርዝር ቁልፍ ትኩረት መስኮች</u>

- የ2ኛ ዙር BPR ለሚተገብሩ ሴክተር መ/ቤቶች ለሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች በክልል አቅም ግንባታ ጋር በመሆን የተሰጠ ሥልጠና ፤
- በዞኑ 12 ወረዳና 3 ከተሞች በሚገኙ 260 ሴክተሮች BPR ለመተግበር 4 ጊዜ የተደረገ ክትትልና ድጋፍ ፤
- ከክልል ተልኮ የተሠራጨ የውጤት ተኮር ማስፈፀሚያ ማኑዋል
- በውጤት ተኮር ዕቅድ አፈፃፀም ሥርዓት ላይ የሰለጠኑ 200 አመራሮችና ባለሙያዎች ፤
- በሁሉም ሴክተር መ/ቤቶች የተደረገ ውጤት ተኮር ዕቅድ /BSC/ አተገባበር 4 ጊዜ የተደረገ ድጋፋዊ ክትትል ፤
- የተገልጋዮች ቅሬታ ለመፍታት የተዘጋጀና የተተገበረ አንድ የተቋቋመ ቻርተር ፤
- የተሠራጨና የእንስፔክሽንና ሱፐርቪዥን መምሪያ ፤
- ለዞን ከተማና ወረዳ 100 አመራሮችና የእንስፔክሽን ቡድን አባላት በእንስፔክሽንና ሱፐርቪዥን ማስፈፀሚያ መመሪያ ላይ የተሰጠ ሥልጠና ፤
- በዞኑ በሚገኙ 314 በፖኬጁ መሠረት የተቋቋመና ሥራ የጀመረ የእንስፔክሽን ቡድን ፤
- በዞኑ የእንስፔክሽንና ሱፐርቪዥን አገ/ት የተሰጣቸው 12 ወረዳዎች ፤
- 4 ጊዜ የተደረገ የእንስፔክሽን ድጋፍ ግብረ-መልስና ሪፖርት፤
- 50% ግለሰቦችና መንደሮችና ቀበሌዎች እንዲመረጡ የተደረገ ቴክኒክ ድጋፍ ፤
- የቀበሌ ም/ቤት የብዙሀኃን ማህበራት እንዲሁም የባህላዊ ተቋማት ተሳትፎን ለማጎልበት 4 ጊዜ የተሰጠ ምክርና ድጋፍ ፤
- በዞንና ወረዳ ደረጃ የተጠናከረ አንድ የምርጥ ተሞክሮ ሰነድ
- የገጠር ልማት ተግባሮች በ314 ቀበሌያት ተጣምሮና ተቀናጅቶ ወደ ተግባር የሚወርድበት የዕቅድ አዘገጃጀት ሪፖርት አቀራረብ አሠራር ፤

- በ314 ቀበሌያት ደረጃ የተዘረጋ የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓት የመረጃና የባለጉዳይ አቀባበል አሠራር ሥርዓት ፣
- በ314 ቀበሌያት ደረጃ አራቱ የልማት ኮሚቴዎች በተቀናጀ ሁኔታ የሚሠሩበትን አሠራር በተጠናከረ መንገድ ማስቀጠል ፣
- በሁሉም በዞኑ ከተማና 314 ገጠር ቀበሌያት የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ እንዲጠናከር የተዘረጋና ሥራ ላይ የተደረገ ድጋፋዊ ክትትል ፣
- እጅ ከፍንጅ ለተያዙ ወንጀለኞች የዕለት ፍርድ ውሣኔ አሠጣጥ ሥርዓት እንዲዘረጋ 4 ጊዜ የተደረገ ድጋፍና ክትትል ፣
- የፍርድ ቤቶች ተደራሽነት / Elitigation/ ቀጣይነት ባለው መልክ ለማስፋፋት 4 ጊዜ የተደረገ ድጋፋዊ ክትትል
- በ3ቱ ሪፎርም ከተማና 314 ገጠር ቀበሌዎች ኮሚንቲ ፖሊሲንግ እንዲጠናከር 4 ጊዜ የተደረገ ድጋፋዊ ክትትል ፣

<u>የተፈፀሙ ዝርዝር ቁልፍ ተግባራት</u>

- በሁሉም መንግሥት ተቋማት መሠታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ እንደተገበረ በታቀደው መሠረት በመጀመሪያ ዙር በ7 ሴክተሮች በተሳካ ሁኔታ ሙሉ ትግበራ የተከናወነ ሲሆን በሁለተኛ ዙር ለሙሉ ትግበራው ጥናታቸውን ያጠናቀቁ 9 ሴክተሮች የሠራተኞች ድልድል በማድረግ ወደ ሙሉ ትግበራ ከ21/1/2002 ጀምሮ በመግባት የተሻለ እንቅስቃሴ ላይ ይገኛል ፡፡
- ሚዛናዊ የውጤት ተኮር ዕቅድ /BSC/ አዘገጃጀትና አሠራርን በተመለተ ጥናቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ በቀድሞ የውጤት ተኮር ዕቅድ አፈፃፀም በ BPR ሴንስ ሳይዛነፍ እንዲተገበር በዞን ፣ 12 ወረዳዎችና 3 ከተሞች ላይ ድጋፍ ተሰጥቷል ፣
- በዞኑ በሁሉም 260 ሴክተሮች ተገልጋዩ ቅሬታ በሰነዱ ላይ በተቀመጠው መሠረት እንደተገበረ ድጋፍ ተሰጥቶ በሁሉም ሴክተር ላይ ተግባራዊ ተደርጓል ፡፡
- በዞኑ በሁሉም ወረዳ ፣ ከተማና ቀበሌ መልካም አስተዳደር ፖኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የእንስፔክሽንና ሱፐርቫይዘር መመሪያዎች ቀደም ሲል የተሠራጨው በሚፈልገው መልክ ተግባራዊ እንዲሆን ድጋፍ በመስጠቱ አተገባበሩ በተሻለ ደረጃ እንዲገኝ ተደርጓል ፡፡
- በሁሉም የዞኑ 314 ቀበሌዎች አመራር 50% በሞዴል አ/አደሮች እንዲመራ ተደርጓል ፡፡

- የቀበሌ ም/ቤት፣ የብዙኃን ማህበራት ተቋማዊ ተሳትፎ እንዲጎለብት በተሰጠው የቴክኒክ ድጋፍ ተቋማዊ ተሳትፎ ጎልቶ እንዲታይ ተደርጓል ፣
- በሁሉም ቀበሌያት ከመልካም አስተዳደር ፓኬጅ አኳያ የገጠር ቀበሌዎች ሥራ አስኪያጆች ከቀበሌ አመራሮች ጋር በተቀናጀ መልኩ ተጣምረው የሚሠሩበት ሂደት ተጠናክረዋል፣
- በሁሉም የዞኑ 3 ከተሞችና 314 የገጠር ቀበሌዎች የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ እንዲጠናከር በተደረገው ቴክኒካዊ ድጋፍ የተሻሉ ምርጥ ተሞክሮዎች ተመዝግበዋል፣

ለማሣያ :- የዳሞት ወይዴ ወረዳ ፖሊሲ በየቀበሌዎቹ ያደረገው አሳታፊ የሥራ እንቅስቃሴ ፣

- በሁሉም የዞኑ የፍትህ ተቋማት የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም አተገባበር ፍትሐዊ ቀልጣፋ ለማድረግ በተሰጠው ድጋፍ የተሻለ አፈፃፀም ተመዝግበዋል፡፡

ማሳያ :- በዱጉና ፋንጎ ወረዳ ፣ በዳሞት ወይዴ በዳሞት ጋሌ እጅ ከፍንጅ ለተያዙ ወንጀለኞች የዕለት ፍርድ ውሣኔ አሰጣጥ ይዘት መጠናከሩና የጎላ ግንዛቤ መፈጠሩ ፡፡

- በሁሉም ወረዳዎች አሳምኖ የማሠራት ባህል መፈጠሩ
- የኅ/ሰቡን ሠላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ ፈጣንና ቀጣይነት ያለውን ፍትሐዊ አገ/ት ለመስጠት በተደረገው ድጋፋዊ ክትትል የተረጋጋ ሁኔታ መፈጠሩ ፣

ማሳያ :- በዳሞት ወይዴ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት የዕለት እስረኛ ቁጥር በየቀኑ መቀነስ /ወንጀለኛ ታሣሪ መጥፋት /

- በሁሉም ወረዳዎች ከኅ/ሰቡ ጋር ተቀናጅቶ የሚሠራ የፖሊስ ኃይሎች ለ314 ቀበሌዎች መመደቡ

3. በአበይት የትኩረት መስክ ፣

- በ3ቱ ሪፎርም ከተማ ማዘጋጃ ቤቶች የሚሠሩ ኮብልስቶን ዝርጋታ ሥራ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ፣
- በዩኒቨርሲቲ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ሥራዎች ላይ የሰጠ ክትትልና ድጋፍ ፣
- የሴክተሩን ሠራተኞች ሥ/የታና ፀረ ኤች አይቪ ኤድስ ለመግታት የተሰጠ ሥልጠና ፣

- ኤች አይቪ ኤድስን በሴክተሩ ሠራተኞች ለመከላከል ለዞንና ወረዳ የተደረገ ድጋፍና ክትትል ፣
- የተካሄደ ሥልጠና ፍላጎት ጥናት ፣
- የተገልጋዮች እርካታ ደረጃ መለኪያ ጥናት ፣
- በዞኑ 12 ወረዳዎችና 3 ከተሞች በስትራቴጂክ ዕቅድ በዓመታዊ ዕቅድና በውጤት ተኮር አሠራር ሥርዓት ለ200 ባለሙያዎች የተሰጠ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና፣

<u>በአበይት የትኩረት መስኮች የተፈፀሙ ዝርዝር ተግባራት</u>

- በምህንድስና አ/ግንባታ ኘሮግራም የግቡን ሴክተር ለማጠናከር በተሰጠው ድጋፍ መሠረት

የዞናችን 3ቱም ሪፎርም ከተሞች ማዘጋጃ ቤቶች በኬቢልስቶን ዝርጋታ የሚሠሩትን የ2002

ዓ/ም. ዕቅዳቸውን ወደ ክልል በመላክ በቅንጅት እቅዳቸውን እንዲተገብሩ ተደርጓል ፣

- የሥርዓተ ፆታንና ኤች አይቪ ኤድስን ሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ በሴክተሩ ዕቅድ ላይ የማካተት ሥራ ተሠርቷል ፣ በተጨማሪም በሥልጠናዎች ለማጠናከር እንዲቻል ምቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ የአጭር ጊዜ ዕቅድ እንዲያዝ ተደርጓል ፣
- ከዞን እስከ ወረዳ /ከተማ በእስትራቴጂክ ዕቅድ በዓመታዊ ዕቅድ ሁሉም የሥራ ሂደቶች እንዲመሩ ድጋፋዊ ክትትልና ግምገማ ተደርጓል ፡

<u>ያልተፈፀሙ አበይት ዝርዝር ተግባራት</u>

- በዩኒቨርሲቲ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ሥራዎች ላይ የተሰጠ ክትትልና ድጋፍ ፣
- የሴክተሩን ሠራተኞች ሥርዓተ ፆታና ኤች አይቪ ኤድስ ለመግታት የተሰጠ ሥልጠና ፣
- ኤች አይቪ ኤድስን በሴክተሩ ሠራተኞች ለመከላከል ለዞንና በወረዳ የተደረገ ድጋፍና ክትትል ፣
- የተካሄደ የሥልጠና ፍላጎት ጥናት ፣
- የተገልጋዮች እርካታ ደረጃ መለኪያ ጥናት ፣

- በዞን በ12 ወረዳና በ3 ሪፎርም ከተማ በእስትራቴጂክ ዕቅድ ፣ በዓመታዊ ዕቅድና በውጤት ተኮር አሠራር ሥርዓት ላይ ለ200 ሰው የተሰጠ ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ፣

**<u>የዕቅድ አፈፃፀም ደረጃ በመቶኛ</u>**

- በቁልፍ ትኩረት መስኮች ተግባራት ከዓመቱ ዕቅድ 32%
- በአበይት ትኩረት መስኮች ተግባራት ከዓመቱ ዕቅድ 32%

**<u>የሰው ሀብት ልማት ዋና የሥራ ሂደት</u>**

**ቁልፍ ተግባር** :- በሰው ኃይል ሥልጠና ማስተባበርና ብቁና አቅም የጐለበተ የሰው ሀብት በማዘጋጀት መልካም አስተዳደር እምርታ ማምጣት

**የታቀዱ ተግባራት** 1. ከክልል በሚደርሰው ሰነድ ለመንግሥት መ/ቤቶች ለዞን ፣ ለወረዳ/ ከተማ አመራር አካላትና ባለሙያዎች ሥልጠና መስጠት

1. የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የትም/ዕድሎች ምልመላና ውድደር ላይ የተከናወኑ የማስተባበር ሥራ ፣

**የተፈጸሙ ዝርዝር ቁልፍ ተግባራት**

1. በ2001 የትም/ዘመን ለ2002 የመደበኛ የትም/ዘመን በኢት/ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በሕግ ፣ በDevelopment Economics & በ public financial management ለ2ኛ ዲግሪ ተወዳድረው ከነበሩት በDevelopment Economic ወደ ኮሌጅ እንዲገባ ላለፈው መሸኛና መገጣጠሚያ ተሰጥቷል፡፡
2. ለመጀመሪያ ድግሪ በ urban planning መገጣጠሚያ ደብዳቤ ተሰጥቶ ትም/ቤት ገብተዋል፡፡

**<u>ያልተፈጸመ ዝርዝር ቁልፍ ተግባራት</u>**

- በተለያዩ ደረጃ የታቀዱ የአመራርና አባላት ሥልጠና አልተሰጠም፡፡

**<u>አበይት ተግባራት</u>**

- ለ2002 የትም/ዘመን አጭርና ረጅም የትምህርት ዕድሎችን ማስተባበር
- በBPR ምደባና ድልድል ያልተመደቡ ሠራተኞችን በትምህርት አማራጭ ለይቶ ማስቀመጥ

## የተፈጸሙ አበይት ተግባራት

- ለ2002 የትምህርት ዘመን በኢት/ሲቪል ሰርቪስ መርሃ ግብር በርቀት ትም/ ኘሮግራም በ Public management ለጀማሪና ለአድቨንስ ስታንዳርድ ውድድር እጩዎች በማወዳደር አቅርበዋል፡፡
- በውጤታቸው መሠረት ያለፉትን ተመዝግበው ትም/እንድጀምሩ የማስተባበር ሥራ ተሠርቷል፡፡
- በ BPR ከተሳተፉ ሠራተኞች መካከል የትም/አማራጭ የሚሆኑት በመመልመል ለክልል ተላልፈዋል፡፡

## የሰው ሀብት መረጃና ስታትስቲክስ አቅርቦት ዐዋና ሥራ ሂደት

### የታቀዱ ተግባራት

### 3.1 ቁልፍ ተግባር

- በዞኑ በየደረጃው በሚገኙ የመንግሥት መ/ቤቶችና ተቋማት ውስጥ የሰው ሀብት መረጃ በአግባቡ ተሰባስቦ ተጠናቅሮና ተተንትኖ በአንድ ማዕከል እንዲደራጁ ማድረግ ነው፡፡

### የታቀዱ ቁልፍ ተግባራት

1. ከተገልጋዮች በሚቀርቡ ጥያቄዎች መሠረት የሴክተሩ የሪኮርድ / ማኀደር አገልግሎት መስጠት
2. በተዘጋጀው የአሠራር ማኑዋልና ፎርማት መሠረት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና መስጠት
3. ከሴክተሩ ተገልጋዮች ለሚቀርቡ የፔርሶኔል መረጃዎች ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት
4. የሰው ሀብት ስታትስቲካል መረጃ በመሳብሰብና በማጠናቀር ለሚመለከተው ማስተላለፍና ለተገልጋዮች ማሠራጨት
5. በወጣው የአሠራር ማኑዋል መሠረት ድጋፋዊ ክትትል ማድረግ

### የተፈጸሙ ዝርዝር ቁልፍ ተግባራት

1. ከተገልጋዮች በሚቀርቡ ጥያቄዎች መሠረት በየዕለቱ በሥራ ሰዓት የሴክተሩ የሪኮርድ /ማኀደር /አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡
2. ከሐምሌ 29/ 2001 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 2/2001 ዓ.ም በክልል አቅም ግንባታ የተሰጠውን መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ / BPR/ እና የሰው ሀብት መረጃና

ስታትስቲክስ አቅርቦትና ዋና የሥራ ሂደት የአፈጻጸም ማኑዋል ወስደን የተለያዩ ቅጻ-ቅጾችንና ሰነዶችን ማባዛት፡፡

3. በሪኮርድ አደረጃጀትና ምዝገባ በኩል ዕለታዊ ሥራዎች ከበፊቱ በተለወጠ መልክ እየተሠራ ይገኛል ፡፡
4. መረጃ በሚፈልጉ ዞን ሴክተር መ/ቤቶችና ክልል /ለጣት አሻራ የሠራተኛ ብዛት ለማወቅ/ ያለውን የዞናችን የተጠና የሰው ኃይል መረጃ ፡፡
5. ክልል ሄደው ሥልጠና የወሰዱ ለሙከራ ትግበራ የተመረጡ ዞን ሴክተር መ/ቤቶችና ቦዲቲ ከተማ ሴክተር መ/ቤቶችን ሙከራ ትግበራ ድጋፋዊ ክትትል፡፡

**ያልተፈጸሙ ዝርዝር ቁልፍ ተግባራት**

በተዘጋጀው የአሠራር ማኑዋልና ፎርማት መሠረት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና መስጠት ፡- ሥራ ሂደቱ ሙከራ ተግበራ ላይ ስላለ ሥልጠናው የሚሰጠው ወደ ሙሉ ትግበራ ስንገባ ነው፡፡

3.2. አበይት ተግባራ

1. ቼክ ሊስት ማዘጋጀት
2. የተሟላ የፔርሶኔል መረጃ በኮምፒዩተር ማጠናቀር
3. የሰው ሀብት ስታትስቲካል መረጃ አጠናክሮ ማሠራጨት
4. ስታንዳርዱን የጠበቀ የመረጃ ማሰባሰቢያ ቅጽ / ፎርማት ማሠራጨት
5. ወቅቱን ጠብቆ የተዘጋጀ የሥራ ሂደት ዕቅድ ማውጣትና ውጤቱን ማቅረብ

የታቀዱ ዝርዝር አበይት ተግባራት

1. ቼክ ሊስት ማዘጋጀት
2. የተሟላ የፔርሶኔል መረጃ በኮምፒዩተር ማጠናቀር
3. የሰው ሀብት ስታትስቲካል መረጃ አጠናቅሮ ማሠራጨት
4. ወቅቱን ጠብቆ የተዘጋጀውን የሥራ ሂደት ዕቅድ ማውጣትና ውጤቱን / ሪፖርቱን/ ማቅረብ፡፡

## <u>የተፈጸሙ ዝርዝር አበይት ተግባራት</u>

1. ቼክ ሊስት አዘጋጅተን ዞን ሴክተር መ/ቤቶችና ቢዲቲ ከተማ ሴክተር መ/ቤቶች ድጋፋዊ ክትትል ተደርጓል፡፡
2. በዞኑ ውስጥ ካሉ 12 ወረዳዎች አቅም ግንባታ ጽ/ቤት የመንግሥት ሠራተኞች አጠቃላይ መረጃ በኮምፒዩተር ተጠናቅሯል፡፡
3. ሙሉ መረጃ ያላቸውንና የሌላቸውን የመለየት ሥራ ተሠርቷል፡፡
4. ከሥልጠና በተዘጋጀ የሥራ ዕቅድ እና ቲም ቻርተር ተፈራርመናል፡፡

4. የዕቅድ አፈጻጸም ደረጃ በመቶ

4.1 በቁልፍ ተግባር በዓመቱ ከታቀደው 25% ተሠርቷል፡፡

4.2 በአበይት ተግባር በዓመቱ ከታቀደው 25% ተሠርቷል፡፡

5. በዕቅድ አፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች
   1. የበጀት እጥረት
   2. የሎጂስቲኮች / material / እጥረት

**6. የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች**

- ሥራ ሂደቱ ወደ ሙሉ ትግበራ ስገባ ወረዳዎችንና ዞን ሴክተር መ/ቤቶች የቅስቀሳ ፣ የድጋፍና የክትትል ሥራ ማጠናከር፡፡

**7. ወደፊት ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች**

የተለያዩ መረጃ መሰብሰቢያ ፎርማትና ማኑዋሎችን በበቂ ኮፒ አባዝተን ማሠራጨትና recent የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ ፣

- ሙሉ ትግበራ ስንገባ ሥልጥና ላልወሰዱ ወረዳዎችና ሴክተሮች ከክልል ጋር በመተባበር ሥልጠና መሰጠት ዕለታዊ ሥራዎችን በመጣው ጥናት ሰነድ መሠረት መሥራት ፡፡

## <u>የሰው ሀብት ሥራ አመራር ዋና የሥራ ሂደት</u>

### <u>የታቀዱ ቁልፍ ተግባራት</u>

- መመሪያዎችን፣ የአፈጻጸም መስፈርቶችን አዘጋጅቶ ማስተዋወቅ ተጠንተው የሚመጡ አዳዲስ የሰው ሀብት ሥራ አመራር አሰራሮችን ማስተዋወቅ
- የሰው ሀብት አስተዳደር የአሰራር ድጋፍና ክትትል ሠነዶችን አዘጋጅቶ፣ የድጋፍና ክትትል አገልግሎት መስጠት፣ ማስተካከያዎችን ማድረግ ግብረ

መልስ መቀበል

- የሰው ሀብት ክፍተት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድና መፍትሔዎችን ማፍለቂያ ተግባራዊነታቸውን መከታተል
- ለደንበኞች የምክርና ድጋፍ አገልግሎት መስጠት

**የተፈጸሙ ዝርዝር ቁልፍ ተግባራት**

- ለሁሉም መምሪያዎች እና ለ3 ከተሞች ደግሞም ለ12 ወረዳዎች የማሟላት አፈጻጸም መመሪያዎችና ደንቦች ተባዝቶ እንዲሰራጭ ተደርጓል።
- ለዞኑ መምሪያዎች፣ ለ12 ወረዳዎችና ለ3 ሪፎርም ከተሞች ለሥራ ሂደቱ አስተባባሪዎችና ፈጻሚዎች ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ተሰጥቷል።
- በሴክተሩ የሰው ኃይል በጉደለባቸው የሥራ ሂደቶች በቅጥር ከሹመት በወረዱ ባለሙያዎች በምደባ እንዲሟላ ተደርጓል።
- የቅጥር ፎርማሊቲ ላይ የተጠቀሱ ርዕሰ ጉዳዮች በጥንቃቄ እንዲሞሉ ተደርጓል
- አገልግሎት የሚያቋርጡ ሠራተኞች መረጃ ተመዝግቦና ተጠናቅሮ እንዲያዝ ተደርጓል። /ለምሳሌ፦ የጡረታ መለያ ቁጥር/

- በዞኑ 12 ወረዳና 3 ሪፎርም ከተሞች የመረጃ አሰባበብና አጠቃቀም፣ የሰው ሀብት ማሟላት አሠራር፣ የድስኘሊን አፈጻጸም / የአገልግሎት ማቋረጥ አሠራርና ሌሎችንም የሰው ሀብት ሥራ አመራር ሥራዎችን በተመለከተ ድጋፋዊ ክትትልና ግምገማ ተደርጓል።

**3.2 ዓብይ ተግባራት**

1. የሥራው ሂደት ባለሙያ ሌሎች የሥራ ሂደቶች ያዘጋጁትን የሰው ሀብት ፍላጐት ዕቅድ ያሰባስባል።
2. ከየሥራ ሂደቱ ታቅዶ የቀረበውን የሰው ሀብት ፍላጐት ዕቅድ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባውን በማስቀደም እንዲሁም ውስጣዊና ውጫዊ አቅርቦትን በማገናዘብ አጠናቅሮ በቅጥር /በዝውውር/ በደረጃ ዕድገት ለማሟላት ለይቶ ያቅዳል።
3. የተዘጋጀውን የሰው ሀብት ዕቅድ ለመ/ቤቱ ኃላፊ አቅርቦ ያጸድቃል።

**የታቀዱ ዝርዝር አበይት ተግባራት**

- የሰው ሀብት ፍላጐት መረዳት
    - የውስጣዊ መረጃዎችን በማገናዘብ ፍላጐትን መረዳት። ይኸም ሲባል

- በጡረታ
- በራስ ፈቃድ
- በድስኘሊን ምክንያት አገልግሎት ማቋረጥ
- በአቅም ማነስ / በሥራ አፈጻጸም ዝቅተኛነት መሰናበት/
- በሞት መለየት
- ለትምህርት ወደ ትምህርት ተቋማት በሚላኩበት ጊዜ
- በረዥም ጊዜ ሕመም ምክንያት
- በወጪድ ምክንያት
- በዓመት ፈቃድ
- በእሥራት ምክንያት

የተፈጸመ ዝርዝር አበይት ተግባራት

- በድስኘሊን ምክንያት አገልግሎት ማቋረጥ
- ለትምህርት ወደ ትምህርት ተቋማት በሚላኩበት ጊዜ
- በዓመት ፈቃድ

ያልተፈጸሙ ዝርዝር አበይት ተግባራት

- ማትጋትና ማበረታታት
- ተሸላሚዎችን መለየትና ማስወሰን
- ዝቅተኛ ውጤት ያመጡ ሠራተኛ ጉዳይ መወሰን
- የመወያያ ሠነድ ዝግጅት

4. የዕቅድ አፈጻጸም ደረጃ በመቶ

4.1. በቁልፍ ተግባር <u>ከዓመቱ ዕቅድ  35%</u>

4.2. በአብይ ተግባራት <u>ከዓመቱ ዕቅድ 32 %</u>

<u>የኢኮቴ አቅርቦትና አገልግሎት ሥራ ሂደት</u>

1.የታቀዱ ቁልፍ የትኩረት መስኮች

1. የመረጃ ልውውጥ ፍልጎት ወይም ክፍተት መለየት
2. ዕቅድ ማዘጋጀት
3. የኢኮቴ መሠረተ ልማት ዝርጋታና ተከላ ማካሄድ
4. መሠረታዊ የኮምፒዩተር ስልጠና መስጠት

5. ጥገናና ሌሎች አገልግሎቶችን መስጠት
6. ሶፍትዌር ዴቨሎፕመንት
7. ድጋፋዊ ክትትል ማድረግ

2. <u>የተፈጸሙ ዝርዝር ቁልፍ ተግባራት</u>

2.1. የመረጃ ልውውጥ ፍልጎት ወይም ክፍተት መለየት

የመረጃ ልውውጥ ክፍተት ለመለየት ጥናት ተደርጓል። በጥናቱ መሠረት የሚከተሉትን መረጃዎችን ሰብስበን ተጠናቅሯል።

በወላይታ ዞን ባሉት ሴ/መ/ቤ/መምሪያ ውስጥ አብዛኛው መምሪያዎች ሙሉ የሆነ መለስተኛ ኮምፒዩተር ስልጠና የወሰዱ የሉም። ያሉትም ፀሐፊዎች ብቻ ናቸው በተጨማሪም አብዛኛው መምሪያዎች የኢንተርኔትና የኢ-ሜይል አጠቃቀም የሚችሉ የሉም። ሆኖም በፋይናንስና በዞን ፖሊስ መምሪያና በጤና መምሪዎች ኢንተርኔት ይጠቀማሉ ሁሉም መምሪያዎች ኔትወርክ አልተዘረጋላቸውም ደግሞም ለሁሉም ሴ/መ/ቤቶች ዌብ-ሳይት የላችውም ከወልማ የተገዙ ኮምፒዩተሮች በፖሊስ መምሪያ ሰባት(7) ሲሆኑ ሁሉም የሚሰሩ ጥሩ ደረጃ ላይ ያሉ ናቸው በግብርና ገጠር ልማት መምሪያ ከወልማ የተገዙ ኮምፒዩተሮች ብዛት 17/አሥራሰባት ሲሆኑ 5 ኮምፒዩተሮች
የማይሰሩ ናቸው።

2.2 የእንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴኪኖሎጅይ መሠረተ ልማት አቅርቦትና አገልግሎት ዋና የሥራ ሂደት የ2002 በጀትና የየሩብ አመቱ ዕቅድ በማዘገጀት ለሚመለከተው አካል ቀርቧል።

2.3. የተሰጡ ጥገናና ሌሎች አገልግሎቶች

1. በታክስ አስተዳደር------------------አንድ ፕሪንተር
2. በዋና አስተዳደር ------------------ሁለት ኮምፒውተሮች
3. በውሃ ሀብት --------------------ሁለት ኮምፒውተሮች
4. በዞን ፖልስ መምሪያ------------ አንድ ኮምፒውተር ሙሉ ጥገናና አራት ኮምፒውተሮች አንቲ ቫይረስ ተጭኖባቸዋል ።
5. በከተማ ልማት ለ2 ኮምፒውተሮች ሙያዊ ድጋፍ በተጠየቅነው መሰረት አድርገናል።
6. በዞን አፌ-ጉባኤ አንድ ፎቶ ኮፒ ማሽን እና ዞን ድርጅት ጽ/ቤት አንድ ፋክስ ማሽን ተጠግነዋል።
7. በዞን ማስታወቂያ የተበላሹ ሁለት ፎቶ ኮፒ ማሽኖች ተጠግነዉ አገልግሎት ላይ ዉለዋል።

2.3. በሁሉም ዞን ሴክተሮች ድጋፋዊ ክትትል ተደርጓል።

በዚሁም ወቅት የኢኮቴ ስራ ሂደት የሚሠራቸውን የስራ ተግባራት የመስተዋወቅ ሥራና የአገልግሎት ቅድመ ሁኔታዎችን የሚገልጽ ፎርማት ተሰራጭቷል፡፡ ማለትም ሴቶች ጉዳይ፣ ጤና ቢሮ፣ፖሊስ፣ዋና አስተዳደር ፣ ፋይናንስ ፣ ግብርና ገጠር ልማት፣ ውሃ ሀብት ፣ስፖርት መምሪያ፣ታክስ አስተዳደር ፣ ማስታወቂያና ባህል፣ንግድ ኢንዱስትሪ፤ከተማ ልማት፣ አፈ-ጉቦኤ፤ት/መምሪያዎች ሁሉ የአገልግሎት ቅድመ ሁኔታና የአገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ ተሰቷቸዋል በተጨማሪም ከኢኮቴ የሥራ ሂደት ስለሚያገኟቸው አገልግሎቶች አጭር የሆነ ማብራሪያ ተሰጥቶዋቸው በዚህም ወቅት በግብርና፣በዋና አስተዳደርና በውሃ ሀብት ኔትዎርክ ለመዘርጋት ፍላጎት እንዳላቸው ገልጸዋል ፡፡

<u>ከወረዳዎችን በቀረበልን ጥያቄ መሰረት</u>

ከኦፋ ወረዳ ለመጡት ሁለት ኮምፒዩተሮች ሙሉ ጥገና ተደርጎለት የተላከ ሲሆን እንዲሁም ስኩል ኔትን በተመለከተ በኦፋ፤ በዴሳ፤ በቦዲቲ፤ በአረካ ከተሞች በሚገኙ መሰናዶ ት/ቤቶች ባለፈዉ ዓመት ችግር የነበረባቸዉ ፕላዝማዎች ጥገና ተደርጎላቸዋል፡፡

**3. <u>ያልተፈፃሙ ቁልፍ ተግባራት</u>**

- የኢኮቴ መሠረተ ልማት ዝርጋታና ተከላ ማካሄድ
- መሠረታዊ የኮምፒዩተር ስልጠና መስጠት
- ሶፍትዌር ዴቨሎፕመንት

4. <u>የዕቅድ አፈጻጸም ደረጃ በመቶ</u>

4.1 በቁልፍ ተግባራት 25%

4.2 በአብይ ተግባራት 25 %

*6. በእቅድ አፈጻጸም ወቅት የገጠሙ ዋና ዋና ተግባሮች*

- በየሴክተሩ ያሉት የአመራር አካላት ስለICT በቂ ግንዛቤ አለመኖር
- በዞናችን ዉስጥ የተለያዩ ስልጠናዎችን ለመስጠት የሚያስችል ለስልጠና የተዘጋጀ ምንም ኮምፒዩተር አለመኖር
- በሴክተሩ በቂ ተሽከርካሪ፤ ለአገልግሎት አሰጣጥ ምቹ የሆነ ቢሮ አለመኖር
- ለሥራዉ መሳካት የሚረዱ የተለያዩ ቁሳቁሶችና ሶፍትወሮች እጥረት
- በአብዛኛው ሴክተር መስሪያ ቤቶች በICT የመደገፍ ስራ አለመሰራት
- የቪዲዮ ኮንፍራንሲንግ ዕቃዎች ብልሽት በአፋጣኝ አለመፈታት
- የስኩልኔት መለዋወጫ ዕቃዎች በቅርቡ አለመገኘት
- የስኩልኔትና ወረዳኔት ኢንተርኔት አገልግሎት መቋረጥ

- አንዳንድ ሴክተር መ/ቤቶች ያለዉን ባለሙያ ትተዉ ከዉጭ መጠቀም

7. የተወሰዱ የመፍቴሄ ርምጃዎች ፡-

- የበጀት ዕጥረት ተፅዕኖን መቀነስ እንዲቻል ዓመታዊ ዕቅዶችን በዝርዝር በማዘጋጀት በወቅቱ ለሚመለከታቸው አካላት በማቅረብና በማስረዳት ተገቢው በጀት እንዲመደብ ጥረት ይደረጋል፡፡ በተመሳሳይም የተሸከርካሪ ችግር እንደሚኖር ታውቆ ያሉትን በቅንጅት የመጠቀም ልምድ እንዲኖር ጥረት ይደረጋል፡፡

- የአመራሩን ግንዛቤ ለማዳበር በየአስተዳደር እርከኑ አጫጭር ሥልጠናዎችና ወርክ ሾፖች ይካሄዳሉ

- የአመራሩ አካላትና ባለሙያዎች በየጊዜው መቀያየርና መልቀቅ በሚመለከት ሠራተኞችና ኃላፊዎች አቅም በመገንባታ ተረጋግተው የሚቆዩበት ሥርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡

- በየደረጃዉ ባሉ ክፍት መደቦች በጀት ተፈልጉ የሰው ኃይል በቅጥርና በዝውውር እንዲሟላ ማድረግ ፤

- በወቅቱ በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራና ኢኮቴ ላይ የግንዛቤ ማዳበሪያ ለሠራትኛውና ለአመራሩ በመስጠት የሚያጋጥሙ ችግሮችን መቅረፍ

8. የወደፊት ትኩረት የሚያስፈልጉ ጉዳዮች፡-

- ለባለ ሙያዎች ወቅታዊ የሆነ የሙያ ስልጠና መሰጠት አለበት፡፡

- ለሥራ መሳካት የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች መሟለት አለባቸው፡፡

- የስልጠና ማዕከል መቋቋም አለበት፡፡

- ሴክተር መ/ቤቶች አዎንታዊ ትብብር እንዲያደርጉ ያስፈልጋል፡፡

## ማጠቃለያ

በመምሪያችን መሠራት የሚባቸውን ቁልፍ የትኩረት መስኮችን በመለየት ግቦች በማስቀመጥና ለግቦቹ ውጤቶችንና ስኬት አመለካቾችን የሚያካትት እንዲሁም የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ተዘርግቶ እየተፈፀመ ነው ፡፡ እስከታችኛው የኅብረተሰብ ክፍል ድረስ ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ለማስፈን የማስፈፀም አቅም ግንባታ ኘሮግራሞችን በተቀናጀ ሁኔታ ማከናወን ቅድሚያ ትኩረት ያደረገ በየደረጃ ለሚገኙ የአቅም ግንባታ ሴክተሮች በመመንዘር እየተገበሩ ናቸው ፡፡ በዚህ መሠረት በ1ኛው ሩብ ዓመት የተከናወኑ ተግባራት ከዚህ በላይ የተገለጹ ናቸው ፡፡